# በድህነት ላይ ሳይሆን በድህ ላይ ዘመቻ!

የወያኔ ነገር ሁሌም የተገላቢጦሽ ሁሌም ሕዝብን ማጥቃትና ማሰቃየት ነውና መሰሎቹ ሁሉ ድርጊታቸው ተመሳሳይና አስከፊ ነው፡፡ በሰሞኑ በሀገራችን ድህ ህብረተሰብ ላይ የተወሰኑ ክፍሎች በወያኔ ቴሌቪዥን ተጠቅመው ያካሄዱት አፀያፊ ዘመቻ ምሳሌ ነው፡፡

ወደ ዝርዝሩ ከመግባታችን በፊት ያለፈውን ለማስታወስ የወያኔ አገዛዝ የሀገሪቷን ኤኮኖሚ አሳድግኩ፤ ምርት ተትረፈረፈ  ወዘተ እያለ የሚቀባጥረው በተጨባጩ ሁኔታ በመጋለጡ ከአዲስ አበባ ከተማ ሁሉ ለምኖና መንገድ አዳሪዎችን አፍሶ ወደ ውጭ በማጓጓዝና በመጣል ለጅብ አጋልጧቸው መመለሱን እናስታውሳለን፡፡ አምባገነኖች በሞላ የግፋቸውን ሀቀኛ ገፅታና ውጤት ለመደበቅ ያለውን ድህነት የሚያንፀባርቁትን በአፈና ለማስወገድ መጣራቸው በተደጋጋሚ በሀገራችንም የታየ ነው፡፡ አፄ ኃይለስላሴ ጊዜ ድሆች ታፍሰው በማጎሪያ በመከታታቸው ተማሪዎች ድህነት ወንጀል አይደለም ሲሉ ያደረጉት የተቃዋሞ ሰልፍ በታሪክ የሚዘከር ነው፡፡ አረመኔው ደርግም ጭራቅ ኢሠፓውን ሊመሰርት ሲነሳ በረሀብ ያልቅ የነበረው ሕዝብ ወደ አዲስ አባባ እንደይገባ አግዶና አጥሮ፤ ስንቱን ሺ የተራበን የሚመግብ ገንዘብን ከአንግሊዝ ሀገር ለሚመጣ ዊስኪ አጥፍቶ ለብቻው አሰረሽ ምቺው ሲል እንደነበር የረሳነው አይደለም፡፡ ወያኔም ስልጣን ከያዘ ጊዜ ጀምሮ በከተሞች ያሉ መንገድ አዳሪዎችንና በልመና ሊተዳደሩ የሚጥሩትን ሁሉ አፍሶ ለማስወገድ በተደጋጋሚ ሲጥር ቆይቷል፡፡

ራሱን አልሻይዳ በሚል ስም እየጠራ ግብረ ሰናይ ነኝ የሚል ተቋም አንድ ተጠሪ ባለፈው ሰሞን በወያኔ ቁጥጥር ሰር ባለው ቴሌቪዥን በሰጠው ቃለ መጠይቅ ቤተክርስቲያኖችና መስጊዶች ደጃቸውን ከለማኞች ማፅዳት አለባቸው ከማለቱ ሌላ የኔ ብጤ እያላችሁ አታሞካሿቸው ሲልም ገስጿል፡፡ የድህነት ምንጭ የሆነውን ስርዓት ከመንካትና ከማውገዝ ይልቅ በሰለባው በእኔ ብጤ ላይ መዝመቱን የመረጡ ረሳቸውን ግብረ ሰናይ የሚሉ አሳዛኞች ብቅ ብለዋል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ የረሀብና የድህነት ሰለባ የሆነው  ከፍጥረቱ የጎደለው ነገር ኖሮ ሳይሆን፤ አንዳንዶች ሊሉ እንደሚቃጡት ሰነፍ ሆኖ ሳይሆን፤ ወይም ምሁር ዶክተር መሆን ያልቻለ መሀይም ሆኖ ሳይሆን በላዩ ላይ የተጫኑበት ርኩሰ ሰው በላ አገዛዞች ሀገሩንና መብቱን  ስለነጠቁትና ስላደቀቁበትና ለረሀብና ድህነት ሰላጋለጡት ብቻ ነው፡፡ በሁኔታው ማፈር ያለበት ሕዝብ ወይ ዜጋ ሳይሆን ገዢ አስተዳዳሪ ነን ብለው የሚመፃደቁትና በሀገር ቤት ሳይሆን በባዕድ ዘንድ አቁማዳ ይዘው የሚለምኑት ሀፍረተ ቢሰ መሪ ተብዬዎች ናቸው፡፡ ድህነት ወንጀል አይደለም፤ ሕዝብን ማደህየት ከወንጀልም አልፎ ለቅጣት የሚዳርግ ሐጢያት ነው ሊባል ይገባል፡፡ የሀገራችን ጨዋ ሰው የኔ ብጤ ሲል ከተበደለውና ከተጎዳው ራሱን አመሳስሎ መከራና ስቃዩን ቢያንሰ በዚህ ደረጃ ሊጋራና የሞራልም ድጋፍ ሊሰጥ እንጂ ሀላፊነት የጎደላቸው እንደሚሉት ድህ መሆንን ሊያዳንቅና ሊያሞካሽ አይደለም፡፡

የወያኔ አገዛዝ ግብረ አበሮችና አዳናቂዎች ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በመደበቅ የሀገሪቷ ኤኮኖሚ በ10 በመቶ አደገ፣ ተመነደገ ብለው ይለፍፋሉ:: የሕዝብ ዕድገት መለኪያው ሌጣ አሀዝ ሳይሆን ወይም ማንም ሊገዛው የማይችለው ሽቀጥ ገዢቆችና መሰሎቻቸው በሚሄዱበት ገበያ መትረፍረፉ ሳይሆን ሌላ ነው:: የሕዝብ የመመገብ ችሎታ ምን ያህል አድጓል? ረሀብ ቀንሷል ወይስ ተወግዷል? የኑሮ ወድነት ጠፍቷል-ቀንሷል ወይስ ጨምሯል? መጠለያ ወይም ቤት አጥቶ መንገድ የሚያድረውና ቤት ሊባል በማይችል መጠለያ ያለው ሕዝብ ቁጥር ቀንሷል? ንፁህ የመጡጥ ውሀና መብራት የሚያገኘው ሕዝብ ቁጥር ጨምሯል? የጤና አገልገሎትስ? በሽታዎችን መቆጣጠር ተችሏል? የትምህርት የዞታስ እንዴት ነው? የሴቶችስ ኑሮ? የህፃናትስ እንክብካቤ? የሰብዓዊ መብት መከበርስ ጉዳይ? ለነዚህና መሰል መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ ዕድገት መኖር አለመኖሩን መመዞርና መወሰኛ ይሆናል እንጂ ገዢው ክፍል ቢንደላቀቅ፣ ፎቅ ቢሰራ፣ ለራሱ ፍጆታ የሚውሉ ሸቀጦችን ቢያስገባ፣ ለጥቂቶች መንደላቀቂያ በሚሊዮን ብር ወጪ ቤቶች ቢሰሩ ወዘተና የዕድገት ደረቅ አሀዝ ቢደረድር ሀገር አደገች ማለት አይቻልም:: 12 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ከዓመት ዓመት የምግብ እርዳታ ተመፅዋች እየሆነ ባለበትየኢትዮጵያ ኤኮኖሚ አደገ ብሎ መለፈፍ ውሸት ማራገብ ነው:: መውደቂያና ስራ አጥቶ ብዙ መቶ ሺ ህዝብ ለአስከፊ ድህነትና ለልመና ተዳርጎ፣ እህቶቻችን ለሴተኛ አዳሪነትና ለዘመናዊ ባርነት ተወርውረው ወዘተ ባለበት ስለ ዕድገት ማውራት ቀልድና ዘበት ነው:: ዕድገቱ የመጣላቸው ጥቂቶች ብቻ ናቸው:: መሰል ጫጫታ የምዕራባውያን ቡችላ መንግስታት ባሉበት ሁሉ የሚደመጥ ሲሆን በነዚህም ሀገሮች ሁሉ ብዙሃኑ መከራው ባሰ እንጂ ሲቀንስ ከቶም አልታየም::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፉት 19 ዓመታት ኑሮው አልተሻሻለም፣ የመብትም ባለቤት አልሆነም:: ይህን አሌ የሚሉ ወያኔዎችና ቅጥረኞቻቸውና ህሊናቸውና ዓይናቸው በግል ጥቅማቸውና ህሊናቸውና ዓይናቸው ሆድ በሚሉት ጉድ የተጋረደባቸው ብቻ ናቸው:: የኔ ብጤው ግን ቁጥሩ ጨመረ፣ ስቃዩ በዛ እንጂ የቀነሰ አይደለም:: መፍትሄው ድህንና ለልመና የተዳረገውን ማሰር ማፈስ፣ ማባረርና በአፋኝ ተቋሞች ማዋከብ ሳይሆን የድህነትን መንስዔና ምንጭ ማድረቅ ነው:: ይህም ማለት ወያኔን ታግሎ መጣልና አገዛዙን ማደባየት ማለት ነው:: አንዳንዶች ከወያኔ አገዛዝ ጋር በኤኮኖሚው መስክ ሊፎካከሩ ወይም በ 2002 ምርጫ ተብዬ አንዲት ወንበር ብቻ ቢደርሳቸውም 15 ና 20 ዓመት ወሰድው ቀስ በቀስ በምርጫ ሂደት የበላይነትን ለመያዝ የሚያልሙ በመሰረቱ ቅዠታሞች መባል ቢገባቸውም ቁም ነገሩ ግን ድህነትና ረሀብ ያጠቃቸው አለመሆናቸው መሆኑም መታወቅ ያለበት ነው:: ሕዝብ ግን ለእንዲህ ዓይነቱ ገዳይ ቧልት ተባባሪ ሊሆን አይጠበቅም:: የወያኔ አገዛዝ ለአንዲት ቀንም ቢሆን በላዩ ላይ እንዲቆይ አይፈልግም:: የተናቀው ድሀ፣ ያጥፋሀ የተባለው ለልመና የተዳረገው ሁሉ፣ ጭቁኑ በአጠቃላይ ተነስቶ መብቱን የሚያስከብር ዕለት ዋ በድህነቱ ላላገጡ፣ ስለ ደኸየ መልሰው ሊያጠቁት ለተነሱና ለፈለጉ:: እውነትም ዋ!

ለም ሀገር ይዘን በረሀብ የምንጠቃው፤ ታታሪ ሕዝብ ይዘን ለችጋር የምንጋለጠው፤ ኩሩ ሕዝብ ሆነን ሳለ ለልመና የምንዳረገው በነበሩትና ባለው አረመኔ አገዛዝ ግፍ፤ ምዝበራና የተዛባ ፈርጀ ብዙ የውድቀት አቅዋምና እርምጃ የተነሳ ነው። ዝምታ የማይበጅ በመሆኑ አደህይተው በተገላ ቢጦሽ ደህ ነህ ብለው ሊያጠፉተ የተነሱት ላይ ሕዝብ መነሳትና በአመፁ አይቀጡ ቅጣትን መስ ጠት አለበት። ገዢዎችና በዝባዦች ህሊናም ይሉኝታም የሌላቸው ሲሆን የወያኔ ደግሞ መረን የለቀቀ አረመኔነት ዋልጌነት መሆኑን ቢያንስ ለ19 ዓመታት ተግተን አውቀነዋል።

ድህነት ወንጀል አይደለም--ወንጀለኛው የወያኔ አገዛዝና ስርዓት ነው!

ድህነትን ለማስወገድ ድህ ያደረግንን የወያኔ አገዛዝ ባመረረ ትግል እናስወግድው!